# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 212 ግንቦት 30 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7፣ ወያኔ በጎንደር በተለይም በሰሜን ጎንደር ላይ እያደረሰ ያለውን በደል በጽኑ ያወግዛል። ልክ እንደ ወልቃይት፣ ጋምቤላ፣ ኦጋዴን እና አፋር ሁሉ ጎንደርም በወያኔ የአፈናና የብዝበዛ መዳፍ ውስጥ መግባቷን ያውቃል።

ግንቦት 7፣ የጎንደር ሕዝብ ዛሬውኑ ከግንቦት 7 ጎን ተሰልፎ በወያኔ ላይ ማመጽ ይኖርበታል ብሎ ያምናል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በያለበት በወያኔ ላይ እንዲያነሳ ጥሪ ያደርጋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ጸረ አማራ ፖሊሲ አራማጅ የሆነውና በቅርቡ በርካታ የአማራ ተወላጆችን ከደቡብ ክልል በቀላጤ ደብዳቤ ያባረረው ሽፈራው ሽጉጤ በሚያደርገው የካናዳ ጉብኝት ታላቅ ህዝባዊ ተቃውሚ ይጠብቀዋል ተባለ

የትግራይን ህዝብ ከአማራ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በሚል የፖለቲካ አላማ ተደራጅቶ በትረ ሥልጣን ለመጨበጥ ድል የቀናው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የአማራን ህዝብ ለመበቀል በሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደመሳሪያ ከሚገለገልባቸው ጀሌዎቹ አንዱ የሆነው የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሽጉጤ የፊታችን እሁድ ለሥራ ጉብኝት ካናዳ ሲመጣ ታላቅ ህዝባዊ ተቃውሞ እንደሚጠብቀው ለዝግጅት ክፍላችን ከተላኩት የተቃውሞ ሰልፍ ዝግጅት ጥሪዎች ለማወቅ ተችሎአል።

በከፍተኛ የሙስና ወንጀል መዘፈቁ በራሱ ፓርቲ ጭምር እየተነገረለት ያለው ሽፈራው ሽጉጤ ወደ ካናዳ የሚመጣው ከክልል ፕሬዝዳንትነቱ ሥልጣን በተጨማሪ የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የቦርድ ሰብሳቢ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት፣ የእርሻ ኮሌጁን ዲንና የተለያዩ ሹመኞችን በመምራት የሳስካቸዋን ዩኒቨርሲቲ እንዲጎበኝ በመጋበዙ እንደሆነ የአድሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ሰሞኑን ባወጣው ዜና ይፋ አድርጎአል።

ሽፈራው ሽጉጤ ራሱ በጻፈ ደብዳቤ የተፈናቀሉ በርካታ የአማራ ተወላጆች የተፈጸመባቸውን ግፍ ሲናገሩ "ነፍሰ ጡር እናት ሌሊት ወልዳ ሲነጋ የሰዓታት ዕድሜ ካለው ልጇ ጋር ከነፍራሿ ደጅ እንደተጣለች፤ ሌሎች ነፍሰ ጡሮች ከቤታቸው በሃይል ተባረው ለስደት እንደተዳረጉ፤ የስምንት ወር ዕድሜ ካላቸው ጨቅላ ሕፃናት ጀምሮ በርካታ ሕፃናት ከሚያጠቡ እናቶቻቸው ጋር አብረው እንደታሰሩ፤ ያመረቱትና በጎተራቸው የሞሉት እህል እያለ የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በረሃብ እንደተጠበሱ፤ በነፍስ ወከፍ እስከ 3ሺህ እግር ቡና ዛፍ፣ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ ፓፓያና ሙዝ የተከሉ እንዲሁም በርካታ የንብ ቀፎ የሰቀሉ ፣ በከብትና በዶሮ እርባታ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ገበሬዎች ያመረቱትንና ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ጥለው ጨርቃቸውን በፌስታል አንጠልጥለው እንዲወጡ መደረጋቸውን ለዚህም የተሰጣቸው ምክንያት 'ምንም ይዛችሁ ስላልመጣችሁ ምንም ይዛችሁ አትሄዱም' እንደተባሉ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መዘገቡ ይታወሳል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በአረብ ሳት የሚሰራጨውን የኤርትራ ቴለቪዥን ሞገድ በማወኩ ከአርብ ሳት ማኔጅመንት ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብቶ የነበረው የወያኔ አገዛዝ ከሳቴላይት ሞገድ ጠለፋ ተግባሩ እንደሚታቀብ በፊርማ በማረጋገጥ የታገዱበትን የቴለቪዥን ስርጭቶቹን ወደ አየር ማስመለሱ ተገለጸ

ከቻይና አገር በውድ ዋጋ ተገዝተው በመጡ የሳተላይት ሞገድ መጥለፊያ መሳሪያዎች የኢሳትን ስርጭት በመጥለፍ የጀመረው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢሳት የሚተላለፉ አንዳንድ ማስረጃዎችን በፕሮግራሞቹ ጣልቃ በማስገባት ያሰራጭ የነበረውን የኤርትራ ቴሌቪዥን ሞገድ በመጥለፉ ከአረብ ሳት ማኔጂመንት ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ እንደገባና ካምፓኒው ለኢትዮጵያ ቴለቪዥን ይሰጥ የነበረውን አገልግሎት በማቋረጥ ከ4 ወራት በላይ ሲወዛገብ ከቆየ በኋላ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ከጁን አንድ ጀምሮ ዳግም ምንም አይነት የሞገድ ጠለፋ ተግባር እንደማያከናውን የተጠየቀውን ውል በመፈረም ወደ አየር እንደተመለሰ ከታማኝ ምንጮች ለማረጋገጥ ተችሎአል።

በኢትዮጵያዊያን ዲያስፖራ የፋይናንስና የሰው ሃይል እርዳታ ከሁለት አመት በፊት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን በአረብ ሳት አማካኝነት ለኢትዮጵያዊያን ተመልካቹ ማቅረብ የጀመረው የቴሌቪዥን ስርጭት በአጭር ጊዜ ውስጥ በርካታ አድናቂዎችን በማትረፉ የተደናገጠው የወያኔ አገዛዝ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት ለማፈን በወሰደው እርምጃ ተከታታይ የሆነ የሞገድ ጠለፋ በማካሄዱ የአረብ ሳት ንብረቱን ለመከላከል ሲል ኢሳትን ከአየር ላይ እንዳወረደና ለ3 አመት ገብቶ የነበረውን የኮንትራት ውል እንዳፈረሰ በወቅቱ መዘገቡ ይታወሳል።

እንደምንጮቻችን መረጃ የአረብ ሳትና ወያኔ መወዛገብ የጀመሩት ኢሳት ከአየር ላይ ከወረደ በኋላም ቢሆን በኤርትራ ቲቪ ላይ ኢትዮጵያን ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ወያኔ የህዳሴ ግድብ ብሎ የሰየመው የአባይ ግድብ ግንባታ ሳይጠናቀቅ መለስ ዜናዊ ከሥልጣን እንዳይወርድ የሚጠይቅ ማስታወቂያ አድስ አበባ ውስጥ እየተለጠፈ መሆኑ ተዘገበ

በሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ የፈነዳው ህዝባዊ አብዮት በአገራችን ውስጥ የፈጠረውን መነቃቃት ተከትሎ ለህዝብ ይፋ የሆነው የአባይ ግድብ ግንባታ ከፕሮፖጋንዳ ፍጆታ አልፎ ምድር ላይ እየተከወነ ያለ ተጨባጭ ነገር ጎልቶ በማይታይበት በአሁኑ ወቅት " አባይን የደፈረ መሪ" ተብሎ በየአደባባዩ ማስታወቂያ የተለጠፈለት ዘረኛው መለስ ዜናዊ ከስልጣን እንዳይወርድ የሚጠይቅ ማስታወቂያ በአዲስ አበባ የተለያዩ ቦታዎች ማስለጠፍ መጀመሩን የግንቦት 7 ዘጋቢ ገለጸ።

መለስ ዜናዊ በተለመደው ቅጥፈቱ ከሶስት አመት በኋላ ሥልጣን እለቃለሁ ብሎ በተናገረ ማግሥት ስልጣን እንዳይለቅ ጥያቄ የሚያቀርብ ማስታወቂያ መሥራት የተጀመረበት ምክንያት እንደ ከዚህ በፊቱ ፓርቲዬ ለምኖኝ ነው እንጂ እኔ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ፍላጎት ኖሮኝ አይደለም ለማለት የታሰበ እንደሆነ ከህዝብ አልተሰወረም ያለው ዘጋቢያችን ፤ ሰሞኑን ለአባይ ግድብ መዋጮ ቃል የገቡት ሁሉ ክፍያቸውን አላካሄዱም የሚል ክሶች በሰፊው እየተሰነዘረ ግንባታው እስኪጠናቀቅ አትህድብኝ የሚል ልመና ለምን በዚህ ሰዓት እንደታሰበ መነጋገሪያ ሆኖአል ብሎአል።

አዲስ አበባ ውስጥ በሚሽከረከሩ መኪኖች ላይ "መለስ የአባይን ግድብ ጅማሮ ሳያጠናቅቁ ስልጣን እይልቀቁ "የሚሉ ባነሮች መለጠፋቸው አንሶ "መሪያችን የጀመሩትን ሳይጨርሱ እንዳይሄዱ እንጠይቅዎታለን።" የሚል ታፔላ ተሰርቶ በአዲስ አበባ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ለመስቀል ዝግጅት እየተደረገ ነው በዘጋቢያችን ሪፖርት መሠረት። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአፋርንና የኢሳ ጎሳዎችን በማጋጨት ከሁለቱም ወገን ከ20 ሰዎች በላይ መገደላቸው ታወቀ

የግንቦት 7 ምንጮች እንደገለጹት ባለፈው ቅዳሜና እሁድ የአፋር ክልል ይዞታ በሆኑት ገዳማይቱ፤ አዳይቱና አንገለሌ ወረዳዎች በአፋርና በኢሳ ጎሳዎች መካከል ወያኔ ሆንብሎ በቀሰቀሰው ግጭት 10 የአፋር ተወላጆችና 9 የኢሳ ተወላጆች ህይወታቸውን አጥተዋል።

በአካባቢው የተሰማራው የፌደራል ፖሊስና በወያኔ ተመልምለው የተለየ ስልጠና ያገኙ መሆናቸው የሚነገርላቸው ልዩ ሃይል ሁለቱ ጎሳዎች ደም የሚያፋስ የርስ በርስ ውጊያ ውስጥ ሲወድቁ ግድያውን ለማስቆም ምንም አይነት እርምጃ እንዳልወሰዱ ታውቆአል።

እንደ መንግሥት የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ ሃላፊነት በእጁ የወደቀው የወያኔ አገዛዝ በንግድ ድርጅትነትና በኢንቨስቴርነት ያቋቋማቸው አካላቱ የተግበሰበሰ ትርፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ሲባል ብቻ ለኢንቨስትመንት አይኑን በጣለባቸው ክልሎች የሚኖሩ ህዝቦች እርስ በርስ እንዲጋጩና በመካከላቸው በሚፈጠረው ቁርሾ መተባበር እንዳይችሉ ለማዳከም ተመሳሳይ ግጭቶችን በየቦታው ሆን ብሎ እንደሚጭር የአደባባይ ምስጥር ሆኖአል።

የአፋር ህዝብ የሰፍረበትን የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ ለስኳር ልማት ለመንጠቅ በተደጋጋሚ ሙከራ ተደርጎ የአካባቢው ህብረተሰብ በፈጠረው ትልቅ ተቃውሞ እውን ለማድረግ ስላልተቻለ እነዚህ ሁለቱን ጎሳዎች ደም በማፋሰስ የትኩረት አቅጣጫ ለመቀየርና ተቃውሞውን ለማርገብ በአፋር ክልል የሰፈረው የወያኔ ሰራዊት አዛዦች ከፍተኛ ሻጥር ሰርተዋል ተብሎአል።

## ባለ አንባሻውን የወያኔ ባንድራ ይዘው እግር ኳስ ሜዳ የገቡ አፍቃሬ ወያኔዎች ባንድራቸውን ተነጠቁ። ጉሽማም ደርሶባቸዋል ተባለ

ለአለም ዋንጫ ማጣሪያ የኢትዮጵያ ብሄራዊ እግር ኳስ ቡድን ከደቡብ አፍሪካው አቻው ጋር ባለፈው ዕሁድ በሮያል ባፎኬንግ ስታዲየም ባካሄደው ጫወታ ላይ አፍቃሬ ህወሃት የሆኑ ግለሰቦች ወደ ስታድዬሙ ይዘውት የገቡት ባለ አንባሻው ባንድራቸውን የተነጠቁት ለአገራቸው ቡድን ድጋፍ ለመስጠት በገቡት ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ነው።

በወያኔ የዘር መድልዎና የፖለቲካ አፈና በአገራቸው ተስፋ ቆርጠው ለስደት ከተዳርጉትና ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ከሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ከሺህ በላይ የሚሆኑት ያለፈውን እሁድ ውድድር ለመሳተፍ በቦታው እንደተገኙ የዘገበው ዘጋቢያችን ፤ የሁለቱ አገሮች ቡድኖች ጫወታቸውን ከመጀመራቸው በፊት ወያኔ የሚጠቀምበት አዲሱ መዘሙር መዘመር እንደተጀመረ ኢትዮጵያዊያኑ ከተቀመጡበት ብድግ በማለት በታላቅ ድምጽ "ኢትዮጵያ የኛ መመኪያ" የሚል ዘፈን ከዳር እስከዳር እንዳቀለጡትና ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ የወያኔ አፍቃሪዎች ወደ ነበሩበት በማምራት የያዙትን ባለአንባሻ ባንድራ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ጎንደር ትጣራለች!!!

ጎንደር በተለይም ሰሜን ጎንደር አደጋ ውስጥ ነች!!!

አምባ ጎርጊስ፣ ደባርቅ፣ ደብር፣ ድብ ባህር፣ ጎልማ፣ ጨው በር፣ አዘዞ፣ ድል አምባ፣ አደዛ፣ አይከል፣ ዋልድባ፣ መገነን እና መተማ ውስጥ እሮሮ በዝቷል!!! ጩኸት በርክቷል!!! እነዚህና ሌሎችም ያልተጠቀሱ የሰሜን ጎንደር መለስተኛና ትናንሽ ከተሞች እና የገጠር መንደሮች የመለስ ዜናዊ አፋኞችና ዘራፊዎች መርመስመሻ ከሆኑ ውሎ አድሯል።

ወያኔ በወለቃይት፣ በጠገዴ፣ በሰቲት እና በሁመራ የፈፀመውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ በሰሜን ጎንደርም ሊደግም ተዘጋጅቷል።

የሰሜን ጎንደር ኢትዮጵያዊ መሬቱን ብቻ ሳይሆን ወጉን፣ ባህሉን፣ ሞገሱን እንዲያጣ እየተደረገ ነው። “ዋልድባ የትግራይ ገዳም ነው” “ራስ ዳሸንም የትግራይ ተራራ ነው” እየተባለ ለጎንደር ህፃናት “ትምህርት” እየተሰጠ ነው። ተከብሮ የቆየው ዋልድባ እየታረሰ ነው። ደባርቅ፣ አምባ ጎርጊስ፣ አዘዞና መተማ እየተበዘበዙ ናቸው። ጎንደር፣ ጎንደሬዎች የሚራቡባት፣ የሚታረዙባት፣ የሚጋዙባት፣ የሚገደሉባት፤ በመለስ ዜናዊ የሚመሩት የትግራይ ገዢዎች ግን የሚፈነጩባት ባድማ ሁናለች።

“የፌደራል ፓሊስ አባላት ነን” የሚሉ የመለስ ዜናዊ ታማኞች በጎንደር ከተማና ገጠሮች እየተዘዋወሩ ዜጎችን ማዋከብ፣ ማንገላታት እና አፍኖ መውሰድ የእለት ለእለት ሥራቸው አድርገውታል። የጎንደር ወጣቶችና አባወራዎች በሰላም ወጥተው መመለሳቸው አጠራጣሪ ሆኗል። መላዋ ጎንደር በተለይም ሰሜን ጎንደር በባዕድ ሠራዊት የተወረረች መስላለች።

ለሃገራቸው፣ ለሕዝባቸው እና ለራሳቸው ትላልቅ ህልሞች ያላቸው ዜጎች እየታደኑ ነው። በነፃነት የሚያስቡ የጎንደር ነዋሪዎች እንዳይኖሩ እየተደረገ ነው። ለነፃነትና ለመብት የሚቆረቆሩ የጎንደር ተወላጆች በየእለቱ በፌደራል ፓሊስ አባላት እየታፈኑ የደረሱበት አይታወቅም። ብዙዎች ተሰደዋል። በውጤቱም ጎንደር አርቆ አስተዋይ እና ታጋይ ልጆችዋን እያጣች ነው።

የጎንደር ገበሬዎች ለተሻለ የመሬት ይዞታ፣ ለማዳበሪያና ለምርጥ ዘር፤ መምህራን ለደመወዝ ጭማሪ እና ለትምህርት ጥራት፤ ምዕመናን የዋልድባ ገዳምን ላለማስደፈር ታግለዋል፤ እየታገሉም ነው። ሆኖም ግን የእስካሁኑ ትግላቸው የመለስ ዜናዊን “የመስፋፋት ፓሊሲን” የሚያስቆም አልሆነም።

እናም ጎንደር ጮሃ ትጣራለች!!! ጎንደር አፍ አውጥታ ትናገራለች!!!

> *መለስ ዜናዊ በወልቃይት የጀመረውን የዘር ማጽዳት ዘመቻ ወደ እኔም እያመጣው ነው!!! ወያኔን አሁኑኑ አስቁሙልኝ!!! ነፃነቴን መልሱልኝ!!! አለበሊያ .... አለበለዚያ ... በወልቃይት፣ በጋምቤላ፣ በኦጋዴን እና በአፋር ከደረሰው የባሰ ፍጅት በኔ ላይ ይደርሳል!!!*

እያለች ነው።

ጎንደር አምርራለች

> *አባወራዎች ታፍሰው ሲወሰዱ፤ ደብር ሲደፈር፤ ታሪክና ቅርስ ሲዋረድ፤ መሬትህ፣ ሃብትህ፣ ጉልበትህ ሲበዘበዝ ምን ትጠብቃለህ? ክብርህን ተነጥቀህ እያለ አንተ ምኑን ሰው ሆንከው? ተነስ!!!*

እያለች ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን በደል በጥልቀት ይከታተላል። ይህ በደል እንዲያበቃ፤ በምትኩም ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና ብልጽግና የሰፈነባት ኢትዮጵያ እንድትመሠረት ይታገላል።

ግንቦት 7፣ ወያኔ በጎንደር በተለይም በሰሜን ጎንደር ላይ እያደረሰ ያለውን በደል በጽኑ ያወግዛል። ልክ እንደ ወልቃይት፣ ጋምቤላ፣ ኦጋዴን እና አፋር ሁሉ ጎንደርም በወያኔ የአፈናና የብዝበዛ መዳፍ ውስጥ መግባቷን ያውቃል።

ግንቦት 7፣ የጎንደር ሕዝብ ዛሬውኑ ከግንቦት 7 ጎን ተሰልፎ በወያኔ ላይ ማመጽ ይኖርበታል ብሎ ያምናል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብም በያለበት በወያኔ ላይ እንዲያነሳ ጥሪ ያደርጋል።

ጊዜ የለንም!!! እንፍጠን!!! ጎንደርን እንታደግ!!! ኢትዮጵያችንን እናድን!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ ጸረ አማራ ፖሊሲ አራማጅ የሆነውና በቅርቡ በርካታ የአማራ ተወላጆችን ከደቡብ ክልል በቀላጤ ደብዳቤ ያባረረው ሽፈራው ሽጉጤ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለዚህ ሁሉ ግፍና በደል ተጠያቂ የሆነው ሽፈራው ሽጉጤ በሌላም በኩል ከየካቲት 5 አስከ የካቲት 11 ቀን 2004 በክልሉ ፓርቲ አማካይነት በተካሄደ የከፍተኛ አመራሮች ግምገማ በከፍተኛ የሙስና ወንጀል እንዲጠየቅ የተበየነበት የህወሓት/ኢህአዴግ ሹመኛ መሆኑን የጋራ ንቅናቄው ባወጣው ዘገባ ገልጾ፤ በመለስና በተከታዮቹ ቋንቋ “ኪራይ ሰብሳቢና ሙሰኛ” የተባለው ይህ ሰው ግምገማ ላይ ለተሰነዘረበት የሙስና ውንጀላ “እኔ ብቻዬን አይደለሁም፤ ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ባለቤት አዜብ መስፍን ጋር በጋራ ገንዘብ ወስደናል፤ የምንጠየቅ ከሆነ ሁለታችንም ህግ ፊት መቅረብ አለብን፤ ብሩን መመለስ ካለብንም ሁለታችንም መመለስ አለብን” ማለቱን አስታውሷል።

የሙስና እመቤት የሚል ቅጽል ሥም የወጣላት የመለስ ዜናዊ ባሌበት አዘብ መስፍን ጋር የጦፈ የንግድ ሽሪክ የሆነው ሽፈራው ሽጉጤ በክልል ደረጃ የተወነጀለበት የሙስና ክስ በዋናው የኢህአዴግ ግምገማ ላይ እንዳይቀርብ የተደረገውና እስካሁን በሥራው ላይ ሊቆይ የቻለው ከአዘብ መስፍን ጋር የላቀ የአክሲዮን ባለ ድርሻ የሆነበት የቡና ንግድ ስላለ የርሱ መጋለጥ ቀዳማዊ እሜቤታችንንም የሚነካ በመሆኑ ስጋት ሰልፈጠረ የግምገማው ወጤት በመለስ ዜናዊ ት ዕዛዝ እንዲገለበጥ በመወሰኑ እንደሆነ ምንጮች ይናገራሉ።

በካናዳ ሳስካችዋን ዩኒቨርሲቲ ለስራ ጉብኝት እንደሚመጣ ፕሮግራም የተያዘለት ሽፈራው ሽጉጤ የሰራውን ሥራ ስለሚያውቅ ጉብኝታቸውን ከተቃውሞ ለመከላከል ሲሉ ምስጢራዊ እንዳደረጉት የገለፁት የጋራ ንቅናቄያችን የደቡብ ምንጮች ምናልባትም የጉብኝታቸው ጉዳይ ይፋ መሆኑን ተከትሎ አቋማቸውን ሊቀይሩ እንደሚችሉም ገምተዋል። አክለውም ሰሞኑን በታላቅ የዓለማችን መድረክ ላይ አቶ መለስ የገጠማቸው አስደንጋጭና ያልተደበቀ መብረቃዊ ተቃውሞ ከፍተኛ የመገናኛ ሽፋን በማግኘቱ የተነሳ አቶ ሽፈራውም ከተመሳሳይ ውግዘት ለመዳን ጉብኝታቸውን በዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች ብቻ እንዲከናወን ሊደርጉት እንደሚችሉም ጠቁመዋል።

## ባለ አንባሻውን የወያኔ ባንድራ ይዘው እግር ኳስ ሜዳ የገቡ አፍቃሪ ወያኔዎች ባንድራቸውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ነጥቀው ምንም ተለጣፊ የሌለውን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ማድረጋቸውን ገልጾአል።

ኢትዮጵያዊያኑ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ሲያወግዙና አፍቃሬ ወያኔዎች ላይ ወረራ ሲፈጽሙ የደቡብ አፍሪካ ፖሊሲ ሁኔታውን በአግራሞት ከመመልከት ውጪ ምንም አይነት ጣልቃ ገብነት አላሳየም ተብሎአል።

ወያኔን በማውገዝና የወያኔ ጀሌዎችን በማሸማቀቅ ለብሄራዊ ቡድናችን ከፍተኛ የሆነ የሞራል ድጋፍ ሲሰጥ የዋለው የደቡብ አፍሪካው ኢትዮጵያዊ ማህበረሰብ ለተጫዋቾቹና አብሮዋቸው ለመጣው ቡድን ባሳየው ወገናዊ ፍቅር ቡድኑ ጫወታውን በራሱ ምድር ያካሄደ ያህል እንዲሰማው እንዳደረጉት ከቡድኑ ጋር ወደ ዚያ አገር ተጉዞ የነበረና ስሙ እንዲገለጽ ያልፈለገ አንድ ተጫዋች ለዘገቢያችን በሰጠው ቃል አረጋግጦአል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በጨዋታው የመጀመሪያ አጋማሽ በ28ኛው ደቂቃ ላይ ሳላሃዲን ሰዒድ ባስቆጠራት ግብ እስከ 78ኛው ደቂቃ ድረስ 1 ለባዶ ሲመራ ከቆየ በሃላ የደቡብ አፍሪካው ካቴልጎ አቤል እምፌላ ባስቆጠራት ግብ አቻ መሆን ችሏል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የመለስ ዜናዊ አገዛዝ አሽቃባጮችና ደጋፊዎች በዚያ አገር ውስጥ እንደከዚህ በፊቱ እንደፈለጉት እንዳይፈነጩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያካሄዱ መሆናቸው ይታወቃል።

በብርሃኔ ገብረክርስቶስ ጥላ ሥር በውጪ ጉዳይ ሚንስትርነት የተሾመው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ግንቦት 7 ከዋሽንግተን ዲሲ ጎዳናዎች ርቆ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ምንም አይነት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ልንፈቅድ አይገባም የሚል የትዕቢት ንግግር ካደረገ ወዲህ ወያኔን አንቀጥቅጥ እንቅስቃሴዎች በአገሪቱ እየተካሄደ መሆኑን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጾአል።

ኢሳት በቅርቡ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ባካሄደው የገንዘብ ድጋፍ ምሽት ላይ ቁጥራቸው ከ2000 ሁለት ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን ከመገኘታቸውም በላይ ለወያኔ አገዛዝ ያላቸውን ጥላቻና ታግለው አገራቸውን ነጻ ለማውጣት ያሳዩት የትግል ስሜት አርአያነት ያለው እንደሆነ በወቅቱ መዘገቡ አይዘነጋም።

## ደም ለማፍሰስ የምትሮጥ እግር፤ ሃሰትን ለመናገር የምትፈጥን ምላስ ወዮውላት !!!

መለስ ዜናዊ ስልጣን ከተቆናጠጠ ግዜ ጀምሮ በአገራችን ዜጎች ላይ ብዙ ውርደት ደርሷል።የብዙ ደጋግና ንጹሃን ዜጎች ደም ፈሷል። ከመለስ ዜናዊ የግድያ መረብ ያመለጡ ደግሞ ለስደት ተዳርገዋል። ይሄ እነ መለስ ዜናዊ የፈጠሩት እውነት ነው።ሌላም እውነት አለ። በእነመለስ ዜናዊ ዘመን በአገራችን ውስጥ አማራ መሆን ወንጀል ሆኗል። ኦሮሞ መሆንም ወንጀል ነው። አኙዋክ መሆንም ወንጀል ነው። ከኦጋዴን ነኝ ማለትም ወንጀል ነው። ጉራጌ መሆንም ወንጀል ነው። በአጠቃላይ በመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት የሚያስከብር የሚያኮራ ሳይሆን የሚያዋርድ የሚያስፈራ ሁኗል።

ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ብዙ ዜጎች ደምና አጥንታቸው እየተቆጠረ ብዙ መከራ ደርሶባቸውል።መጀመሪያ በአማራው ላይ ብርቱ ዘመቻ ተደረገ።አማራው አብሮ ከኖረው ህዝብ ጋር እንዲጋጭ ሁኖ ብዙ ንጹሃን ዜጎች ደም በከንቱ ፈሰሰ። ብዙዎችም ይሄ አገራችሁ አይደለም ወደ አገራችሁ ሂዱ ተብለው ለዘመናት ከኖሩበት መንደር ተነቅለው ያፈሩትን ንብረት እየተው አውላላ ሜዳ ላይ ተጣሉ። ”አማራ የትግራይ ዋነኛ ጠላት ነው” ብለው መጽሃፍ ጽፈው አማራ ብለው በጠረጠሩት ላይ ሁሉ የበቀል ሰይፋቸውን እንደመዘዙ እስከ ዛሬ ዘለቁ። ይሄ የዚህ ዘመን የመለስ ዜናዊ ገድል ነው።

የመለስ ዜናዊ የበቀል ሰይፍ በአማራ ላይ ብቻ አልተወሰነም። ኦሮሞውም የእነመለስ የበቀል ሰይፍ ከሚያርፍባቸው ዜጎች መካከል ዋነኞቹ ሁነዋል። ድምጹን ከፍ አድርጎ “ኦሮሞ ነኝ” ያለ ሁሉ ኦነግ ነው እየተባለ የመከራ እንጀራን እንዲበላ፤ የመከራ ጽዋንም እንዲጠጣ ወደ እስር ቤት ተጋዘ። በቃሊት ወይኒ ቤት የታሰሩ ኦሮሞዎችን ብዛት ያዩ አቶ ስየ አብርሃ “የቃሊት ወይኒ ቤት ጣሪያውና ግድግዳው ኦሮሚኛ ይናገራል” ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። የኢትዮጵያ እስር ቤቶች በኦሮሞዎች የመጣበባቸው ሚስጥር እራሳቸውን ለመለስ ዜናዊ ጥቅም አስከባሪነት ካሰለፉት ከነ ባጫ ደበሌ ወይም አባዱላ ገመዳ ተርታ ለማሰልፍ ፍቃደኛ ያልሆኑትን ሁሉ በኦነግነትና በጸረ ወያኔነት ለመፈረጅ በተከሄደበት መስመር ነው። በጄሌነት ማገልገል ያልፈለጉ ወይም ለመለስ ዜናዊ ሹምባሽነት ያልፈቀዱ፤ ይልቁንም በኦሮሞነታቸው ኮርተው ለራሳቸው ክብር የቆሙ ሁሉ በየእስር ቤቱ ተዘግቶባቸው አስታዋሽ አጥተው ቀርተዋል። ብዙዎች የደረሱበት ሳይታወቅ እንዲጠፉ ተደረጓል። መለስ ዜናዊ ያተረፈልን ይህን የመሰለውን ስቃይና መከራ እንጂ ሌላ አይደለም።

የመለስ ዜናዊ ጠላቶች አማሮችና ኦሮሞዎች ብቻ አይደሉም። ኦጋዴኖችና አኙዋኮችም በመለስ ደም በለበሱ የጥላቻ ዓይን የሚታዩ ናቸው። ኦጋዴን ሰው አልባ እስከትሆን ድረስ እልቂት ተፈጽሞባታል። ወንዱን ከሴቱ፤ ወጣቱን ከአዛውንቱ ሳይለዩ ግድያ ፈጽመዋል። ጎጆአቸው ተቃጥሏል።ሴቶቻቸውም ተደፍረዋል። አረጋዊያን ተዋርደዋል። በዚህም ድርጊቱ መለስ ዜናዊ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች በኩል በሰው ዘር ላይ ወንጀል በመፈጸም እጁ ተይዞ ለፍርድ እንዲቀርብ ጥያቄ ቀርቦበታል። ይሄ ብቻም አይደለም በጋምቤላ የተፈጸመውን ማየትና መስማት በእጅጉ የሚዘገንን ነው። በአንዲት ጀንበር አራት መቶ ሰዎች ተገድለው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበሩ ተደርጓል። ተይዘው ብልቶቻቸው ተቀጥቅጦ ዘር እንዳያፈሩ የተደረጉም ብዙ ናቸው። አኙዋክን ለማሰቃየት “ተርብ ሻለቃ” የተባለ የሰው ልጆች ማሰቃያ ስፍራ በመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን ተቋቁሟል። እዚህ “ተርብ ሻለቃ” የተባለ ቦታ የገባ ዜጋ ዳግም የጸሃይን ብርሃን አያይም። እዚህ ተርብ ሻለቃ ውስጥ ሰዎች በህይወት እንዳሉ በእሳት እንዲቃጠሉ ይደረጋል። በኤለክትሪክ ሞገድ እንዲሰቃዩ ይሆናል። በውሃ እንዲታፈኑ ተደርጎ ያደረጉትንም ያላደረጉትንም እንዲናዘዙ ግድ ይባላሉ። ከዚህ ኑዛዜ በኋላ በህይወት እንዲኖሩ እድል ፈንታ አይሰጣቸውም። ይሄ ሁሉ መለስ ዜናዊ በሚመራው ህወሃት በተባለ ዘረኛ ድርጅት ይፈጸማል።

መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ካለው ጥላቻ የተነሳ አገሪቷን አገር ሊያሰኙ የሚችሉ የጋራ እሴቶችን ሁሉ ለማፈራረስ የቻለውን ሁሉ አድርጓል። በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ እጁን በማስገባት ተቋማቱን ከፋፍሎ የምእመናኑን ህብረት አፍርሷል። ትላንትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ውስጥ እጁን በማስገባት አንዲቷ ቤተክርስትያን ለሁለት እንድትከፈል ምክንያት ሁኗል። ዛሬ ደግሞ በሙስሊሞች መካከል ገብቶ የምታመልኩትን እኔ አውቅላችኋለሁ እያለ ነው። የለም እኛ የምናመልከውን እናውቃለን ያሉ ምእመናንን አሸባሪዎች፤ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ፍላጎት ያላቸው ናቸው ሲል ደንፍቷል። ለዚህም ከቶን በላይ ማስረጃዎች አለኝ ቢልም አንዲት ማስረጃ እንኳ አቅርቦ ሊያሳይ አልቻለም። ክርስትያኑም ሙስሊሙም እንደሚያውቀው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የአክራሪነትም ሆነ የአሸባሪነት መንፈስ የለባቸውም። የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጥያቄ ወያኔ የገነባውን የብሄረሰብ አጥር ሰብሮ አላህ የፈጠረው ሁሉ በወንድማማችነት ተከባብሮ የሚኖርበት ሥራአት ይኑረን፤ የእምነት ነጻነታችን ይከበር፤ በሃይማኖታችን ጉዳይ ጣልቃ ገብነት ይቁም አሉ እንጂ እስላማዊ መንግስት፣ እንመስርት የሚል አይደለም። በብሄር እንደማይከፋፈሉ ሲታወቅ በእምነት መስመር እንዲከፋፈሉ የተዘየደባቸውን አንቀበልም አሉ እንጂ ለዘመናት አብረውት ለኖሩት ክርስቲያን ወገኖቹ ስጋት የመሆን ፍላጎት እንደሌላቸው የቆየው ታሪካችን ምስክር ነው። ጥያቄያቸው ቢለጠጠ እንኳ ሰብዓዊ መብት የሚያከብር መንግስት ይኑረን ፤ ዘረኝነት ለማናችንም አይበጀንም ከማለት የዘለለ እይደለም።

ይህ ሁሉ እየሆነና አገሪቷ በብዙ መከራ ውስጥ ባለችበት በዚህ ዘመን እያያችሁ ዘረኝነትንና ዝሪፊያን ይሁን ይደረግ ያላችሁ ወዮታ አለባችሁ።እንዲህ ዓይነት ውረድት በኢትዮጵያ አገራችሁ ሲፈጸም ዓይታችሁ እንዳላያችሁ፤ ሰምታችሁም እንዳልሰማችሁ የምትሆኑ በታሪክ ተወቃሾች ናችሁ። አገሪቷ እንዲህ ስትመሳቀል ልጆቻችሁ የት ነበራችሁ ቢሏችሁ ምንም መልስ አይኖራችሁም። የታሪክ ወቀሳ ከዚያ ይጀምራል። ጭቆናው፤ ሙስናው፤ ዘረኝነቱ በዚህ ትውልድ ባለማብቃቱም ልጆቻችን የዚህ ክፉ ሥርዓት ተገዥ ሆነው መኖር እድል ፈንታቸው ይሆናል። የጥቂት ዘረኞችና ዘራፊዎች ልጆች በብዙሃኑ ዜጎች ልጆች ተንደላቀው በታላላቅ ዩንቨርስቲዎች ተምረው ለገዥነት ሲዘጋጁ የብዙሃኑ ልጆች ራሳቸውን ለተገዥነትና ለሌላ ስቃይ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ግድ እየሆነባቸው ነው።

እንዲህ ዓይነቱን ክፉ ሥርዓት መቀየር የህልውናችን አብይ ጉዳይ ነው።ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አባላት የመለስ ዜናዊን ዘረኛ እና ዘራፊ ሥርዓት ከስልጣን ሳያወርዱ ለሽፋሽፎቻቸው እንቅልፍ፤ ለነፍሳቸው እረፍት አያደርጉም። ጥቂት ዘረኞች ሁላችንንም ተጭነው ብዙሃኑም ዘረኞችንና ዘራፊዎችን ተሸክመው የምንኖረበት ሥርዓት ሳያበቃ አናርፍም።

ህዝብ ለነጻነቱ የሚያደርገውን ትግል ወያኔ እንዲጨፈልቅ መረጃ የምታቀብሉ፤ ሃቀኛ ዜጎች ሲወነጀሉ የሃሰት ምስክርነት የምትሰጡ እና ታዛችሁ የንጹሃንን ደም ለማፍሰስ የምትፋጠኑ፤ ሁሉ ከዚህ ተግባራችሁ በመታቀብ ከነጻነት ትግል ጎራ መሰለፊያው ጊዜ አሁን ነው። ይህን ካልሰማችሁ ወዮውላችሁ እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

**እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ !!!**

## ወያኔ የህዳሴ ግድብ ብሎ የሰየመው የአባይ ግድብ ግንባታ ሳይጠናቀቅ መለስ ዜናዊ ከሥልጣን

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ይህ በዚህ እንዳለ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ ሥራ ተቋራጮች ለህዳሴው ግድብ ቃል ከገቡት ውስጥ የሰጡት 10 በመቶውን ብቻ በመሆኑ አቸኳይ ስብሰባ ተጠርተው እንደነበረ ታወቀ

በተለያዩ የኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ሥራ ተቋራጮች ለህዳሴው ግድብ ቃል ከገቡት 150 ሚሊዮን ብር ውስጥ እስካሁን የለገሱት 10 በመቶውን ማለትም 15 ሚሊዮን ብር ብቻ እንደሆነ ሲታወቅ በስብሰባው የተገኙት ተቋራጮች” መንግስት ፕሮጀክቶችን ሁሉ ለቻይና እና ለጃፓን ተቋራጮች እየሰጠ ባለበት ሁኔታ መሥራት አልቻልንም” ሲሉ ተቃውሟቸውን ማሰማታቸው ተረጋግጦአል።

ግንቦት 25 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ ባህልና ቴአትር አዳራሽ በተደረገው በዚሁ ስብሰባ ላይ የሥራ ተቋራጮቹ አገርን የሚመለከት ማንኛውንም ዓይነት ነገር ሲመጣ ግንባር ቀደም ሆነው ቢቀርቡም፣ መንግሥት ግን አንድ የኮንስትራክሽን ሥራ ለማሠራት ሲፈልግ፣ ፕሮጀክቱን የሚሰጠው ለቻይናና ለጃፓን ተቋራጮች መሆኑን በማማረር ተናግረዋል፡፡

ወያኔ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማሮቶ የሚገኘውን ኢትዮጵያዊ በሙሉ ከአቅሙ በላይ ግብርና የተለያየ መዋጮ እያስከፈለ በኢንቨስትመንት ስም ተጠቃሚ የሆኑት ግን ለወያኔ ባለስልጣናት ከፍተኛ የሆነ መደለያ በውጪ ምንዛሪ የሚሰጡ ህንዶችና ቻይኖች እንደሆነ ይታወቃል።

## የሀሮማያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ባነሱት የአካዳሚ ጥያቄ ከፉኛ ድብደባ ተፈጸሞባቸዋል ተባለ። ዩኒቨርሲቲው በፖሊስ ተወሮ የመማር ማስተማር ሥራው ተስተጓጉሎአል

በሃሮማያ /ዓለማያ/ ዩኒቨርስቲ በቴክኖሎጂ ፋኩሊቲ ውስጥ የሚገኘው "የወተር ኢንጂነሪንግ" ዲፓርትመንት የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች ባነሱት አካዳሚክ ጥያቄ ሳቢያ ፌዴራል ፖሊስ ወደ ዶርማቸው ገብቶ ስለደበደባቸው በርካታ ተማሪዎች ተጎድተዋል ሲል የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት ዘገበ።

መብታቸውን የጠየቁ ተማሪዎች ለሁለት ቀናት የመመገቢያ ካርዳቸውን ተነጥቀው ምግብ እንዳያገኙ ተደርጎአል ያለው የኢሳት ዘገባ፤ ዩኒቨርስቲው ሙሉ በሙሉ በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ጥበቃ ሥር እንደሚገኝ ገልጾአል።

ተማሪዎቹ "በሀገሪቱ ያሉ ሌሎች ዩኒቨርስቲዎች ይህን የትምህርት ዘርፍ "ሃይድሮሊንክ" በሚል ሥያሜ የሚሰጡ ቢሆንም ለእነሱ ደግሞ ተመሳሳይ ትምህርት እያጠኑ ወተር ኢንጂነሪንግ ተብሎ መሰየሙ በሥራ ዓለም ላይ ያላቸውን ተፈላጊነት በ75 በመቶ እንደቀነሰባቸው ይናገራሉ።

ተማሪዎች ባነሱት አካዳሚክ ጥያቄ ዲፓርትመንቱ ካልፈለጋችሁ ጊቢውን ለቃችሁ ውጡ በማለቱ ጥያቄው ተካሮ ሁሉም የዲፓርትመንቱ ተማሪዎች አንመዘገብም በማለታቸው ባለፈው አርብ የፌዴራል ፖሊስ ዩኒቨርስቲውን ከብቦ ወደ ወስጥ በመዝለቅና ወደ መኖሪያ ግቢያቸው በመግባት በቆመጥ ተማሪዎችን በመደብደቡ በርካታ ተማሪዎች መፈንከታቸው ተረጋግጠዋል ብሎአል ኢሳት።

የፌዴራል ፖሊስ አባላት በተማሪ የደህንነት ኋይሎች እየተመሩ ከሁለተኛ እስከ አምስተኛ ዓመት የደረሱ የዲፓርትመንቱ ተማሪዎች ወደ ሚገኙበት ክፍል በመግባት በቆመጥ በመቀጥቀጥና በማንበርከክ የመመገቢያ ካርዳቸውን ለሁለት ቀናት እንደነጠቁዋቸውና እንዳስራቡዋቸው እንዲሁም ከግቢው ወጥተው የነበሩ ተማሪዎችን ፖሊስ መልሶ እንዳይገቡ በመከልከል ውጭ እንዲያድሩ እንዳደረጋቸው ተዘግቦአል።

በፖሊስ እርምጃ የተቆጡት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉ ሲሆን፣ የተማሪዎቹ ጥያቄ ፖለቲካዊ አቅጣጫ እንዳይዝ በመፍራት ፌዴራል ፖሊስ ጊቢውን ተቆጣጥሮታል ተብሎአል።

## የወያኔ ፌደራል ፖሊስ አባላት በደባርቅ እና በጭልጋ ወረዳዎች ሁለት የተቃዋሚ ፓርተዎች አባላትን አፍነው መውሰዳቸው ተዘገበ

ወያኔ በሰሜን ጎንደር እያካሄደ ያለውን አፈና በማጠናከር በምርጫ 97 ወቅት ቅንጅትን ወክሎ በደባርቅ ወረዳ የተወዳደረውንና በምርጫ 2002 ደግሞ አንድነት ፓርቲን በመወከል ሲንቀሳቀስ የነበረውን አቶ ስለሺ ጥጋቤ የተባለን ዜጋ ከትናንትና በስቲያ ሃሙስ ከመኖሪያ ቤቱ አፍነው መውሰዱን ለግንቦት 7 የደረሰ መረጃ አጋለጠ።

እንደ መረጃ ምንጮቻችን ዘገባ ግለሰቡ ከተያዘ በሁዋላ ቤቱ ለ2 ሰአታት ሲበረበር እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል። ለአቶ ስለሺ ጥጋቤ ቅርብ የሆኑ የዜና ምንጭ እንደገለጡት፣ ከ10 በላይ የሚሆኑ ፖሊሶች እና የደህንነት ሰዎች ግለሰቡን አፍነው ወደ አልታወቀ ቦታ ወስደውታል።

በጭልጋ ወረዳም እንደዚሁ የመኢአድ አደራጅ የሆነው አቶ መለሰ አስሬ በመለስ ዜናዊ ጸጥታ ሰራተኞች ቤቱ ሲፈተሽ ከቆየ በሁዋላ ወዳልታወቀ ስፍራ ተወስዷል።

ግለሰቦቹ ታፍነው ስለተወሰዱበት ምክንያት እና የት እንዳሉ ለቤተሰቦቻቸውም ሆነ ለቅርብ ጋደኞቻቸው የተገለጸ ነገር ባይኖርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአካባቢው እያየለ በመጣው ህዝባዊ ተቃውሞና ህብረተሰቡ በክልሉ ለሚንቀሳቀሰው ታጣቂ ሃይል እያሳየ ያለው ወገንተኝነት የአገዛዙን ሹሞች እያሳሰበ በመምጣቱ በተቃዋሚነት የሚታወቁትን ሰዎች በማሰርና በማሰቃየት የበለጠ መረጃ ሊገኝ ይችላል ከሚል ስሌት እንደታፈኑ ለወያኔ ደህንነት ቅርበት ያላቸው ምንጮች ይናገራሉ።

የደባርቅ ወረዳ ወጣቶች ከዋልድባ ገዳምና የራስ ደጀንን ጋር በተያያዘ ውዝግብ፣ እንደሁም ከመልካም አስተዳዳርና ፍትህ እጦት ጋር በተያያዘ ከአካባቢው ባለስልጣናት ጋር በተደጋጋሚ እንደሚላተሙ መዘገቡ ይታወቃል። የደባርቅና የጭልጋ ወረዳ መምህራን በቅርቡ የደሞዝ ጭማሪ ይደረግልን በማለት ተቃውሞ ካሰሙ መምህራን መካከል ቀዳሚዎቹ እንደነበሩና ላነሱት ጥያቄ ከሥራ እስከመባረር መድረሳቸው በተደጋጋሚ ተዘግቦአል።

## በአረብ ሳት የሚሰራጨውን የኤርትራ ቴለቪዥን ሞገድ በማወኩ ከአርብ ሳት ማኔጅመንት ጋር

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አስመልከቶ የሚቀርቡ አንዳንድ ወያኔን ወንጀል የሚያጋልጡ መረጃዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ከተሰራጩ አፍኖና አደንቁሮ ለመግዛት የሚደረገውን የመለስና ግብረአበሮቹን ጥረት የሚጻረር ሆኖ በመገኘቱ እንዲህ አይነት የሞገድ ጠለፋዎች እንዳይደረጉ የሚከለክለውን አለም አቀፍ ህግ በመጣስ የጠለፋ ተግባሩን በመቀጠሉና ካምፓኒው የአረብ ሳት ለኢትዮጵያው አገዛዝ ከዚህ ተግባሩ እንዲታቀብ በተደጋጋሚ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ ከቁብ አለመቁጠሩ ከተረጋገጠ ቦኋላ ነው።

በወያኔ ተግባር የተማረረው የአረብ ሳት ለወያኔ ቴለቪዥን ጣቢያ ይሰጥ የነበርውን አገልግሎቶች ሁሉ በማቋረጥ ወያኔ ለአለም አቀፍ ህግ ተገዥ እንዲሆን ካልሆነ ጉዳዩን ለአለም አቀፍ የቴሌኮሚኒከሼን ህብረት በመውሰድ ክስ እንደሚመሰርትበት ማስጠንቀቂያ እንደሰጠ የገለጹ ምንጮች በበረከት ስምን የሚመራ ከፍተኛ ልዑካን ቡድን በተደጋጋሚ ከአረብሳት አመራር ጋር ለመደራደር ወደ ዱባይ ተመላልሶ እንደነበር ገልጸዋል።

በመለስ ዜናዊ የተላከው የወያኔ ልዑካን ቡድን ከአረብ ሳት ጋር ባደረገው ድርድር ኢሳትን የመሳሰሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች ዝግጅቶች በአረብ ሳት በሚተላለፈው የኤርትራ ቴሌቪዥን ላይ የማይቀርቡ ከሆነ፣ ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሚተላለፈው ማንኛውም አይነት የተቃዋሚዎች ስርጭት ለማቋረጥ መንግሥታቸው ዝግጁ መሆኑን በቅድመ ሁኔታ አቅርቦ እንደነበር ሆኖም የኤርትራ መንግስት ቅድመ ሁኔታውን ለመቀበል ፍቃደኛ እንዳልሆነ ታውቆአል። የኤርትራ መንግስት በወያኔ በኩል ለቀረበው ቅድሜ ሆኔታ የሰጠው ቃል "ወያኔ ወደ ኤርትራ የሚልከውን የተቃዋሚ ስርጭት ከፈለገ ከአንድ ሰአት ወደ 24 ሰአት ማሳደግ እንደሚችል እና በስርጭቱ ምንም አይነት ተቃውሞ እንደሌለው፣ ነገር ግን በራሱ ጣቢያ ላይ ለሚተላለፉ ዝግጅቶች ከራሱ ውጪ ማንም ሃይል ሊወስንለት እንደማይችል በግልጽ እንደገለጸ ምንጮች ገልጸዋል።

እንደ መረጃ ምንጮቻችን ዘገባ በወያኔ አገዛዝ አቋም የተበሳጩት የአረብ ሳት ባለስልጣናት ለ4 ወራት ያክል በራቸውን በመዝጋት ማንንም የወያኔ ባለስልጣን ለመቀበል አሻፈረን ብለው ነበር። በአረብ ሳት ውሳኔ የተደናገጡት የወያኔ ባለስልጣናት ከአራት ወራት ልመና በሁዋላ ለአረብ ሳት ባለስልጣናት ከአሁን በሁዋላ አፈና እንዳማያካሂዱ የጽሁፍ ማረጋገጫ በመስጠታቸው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ወደ አየር እንዲመለስ ተፈቅዶለታል ተብሎአል።

አንድ የአረብ ሳት ባለስልጣን ከኢትዮጵያው አገዛዝ ባለስልጣናት ጋር ከተገናኙ በሁዋላ በባለስልጣኖቹ ድርጊት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ሁኔታ ማዘናቸውን መናገራቸውን ምንጮች አስታውቀዋል። የኤርትራ ቴሌቪዥን የኢሳትን ስርጭት ከኢንተርኔት ላይ በመውሰድ አልፎ አልፎ እንደሚያሰራጭ ይታወቃል።

አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶችና የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅቶች የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፕሬሱን ለማፈን የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በተደጋጋሚ አውግዘዋል። የመለስ መንግስት ግን ሳተላይት ስርጭቶችን ከማፈን አልፎ በአገር ውስጥ የሚታተሙ አነስተኛ ስርጭት ያላቸውን ጋዜጦች ሳይቀር ለመቆጣጠር አዲስ የማተሚያ የንግድ ውል ማውጣቱ ይታወቃል። በኢንተርኔር የሚሰራጩትን መረጃዎች ለማፈንም አዲስ የቴሌ ህግ በማርቀቅ ላይ ይገኛል። 99 ነጥብ 6 በመቶ የሆነ የህዝብ አመኔታ አግኝቼ ተመርጫለሁ የሚለው የመለስ መንግስት፣ ነጻ ሀሳብን ከሚያፍኑ የአለም አገሮች መካከል በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፦ በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>፦ በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
<u>ማሳሰቢያ</u>፦ ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org